ከላይ በገለጥነው መሠረት እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስን አደራ ፍጹም አምነውና አክብረው የተቀበሉ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች የቃል ኪዳን እናታቸው የሆነችውን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን በዘወትር የምስጋና ጸሎታቸው "ተፈሥሒ ኦ ቅድስት እሞሙ ለኵሎሙ ሕያዋን ናንቀዐዱ ኀቤኪ ትስእሊ በእንቲአነ፤ በመንፈስ ልደት የከበሩ ቅዱሳን ሕያዋን የሆኑበት ማየ ገቦ የተገኘብሽ፣ የሕያዋን ጻድቃን እናታቸው ንዕድ፣ ክብርት እመቤታችን ደስ ይበልሽ፤ አንድም በቅዱስ ዮሐንስ አንጻር ልጆችሽ የምንሆን እናታችን ድንግል ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ:: ወደ ልጅሽ ወደ ወዳጅሽ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ትለምኚልን ዘንድ ዓይነ ኅሊናችንን ወደ አንቺ እናነሣለን»(400) እያሉ ዘወትር ያከብሯታል፤ ያመሰግኗታል፤ ይማጸኑባታልም::

ዳግመኛም ቀዳሚት ሔዋን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመታመኗና ባለመታዘዟ ምክንያት የእግዚአብሔርን ጸጋ ስለተገፈፈችና የልጅነት ጸጋዋንም ስላጣች በምትኩ የቅጠል ልብስን ለራሷ አደረገች:: በአንጻሩ ደግሞ አዲሲቷ ሔዋን እመቤታችን ሁሉን በጸጋ ለሚያለብሰው ለወልደ እግዚአብሔር ንጹሕና ቅዱስ የሆነውን ሥጋዋን የከበረ ልብስ ይሆነው ዘንድ ሰጥታለች:: ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢር አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ እመቤታችንን ባመሰገነበት ቅዳሴው «ምዕናምሙ አንቲ ዘእምኔኪ ለብሰ አማኑኤል ልብሰተ ሥጋ ዘኢይትረኰም፤ የማይመረመር አማኑኤል የሥጋን ልብስነት ካንቺ የለበሳት የድኅነት መሣሪያው አንቺ ነሽ»(401) ሲል መስክሮላታል::

ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በዚህ የወላዲተ አምላክነት ጸጋዋ በድቀተ ኃጢአት የነበረው መሳው የሰው ዘር ወደ ቀደመው ክብሩ የተመለሰባትና ወደ ጥንተ ርስቱ የገባባት ምክንያተ ድኅነት፣ መሠረተ ሕይወት ናት:: በመሆኑም በምሥጢረ ድኅነት ውስጥ ጎልቶ

(400) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 58-59::

(401) *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 64:: Palmer, *Mary in the Documents of the Church,* 53.



የምናየው ይህ የእመቤታችን ልዩ ሱታፌ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በሰፊው ለሚዘመረውና "አካሲስቶስ ምስጋና" ["Akathistos (Non-Sitting) Hymn"](402) በመባል ለሚታወቀው ኦርቶዶክሳዊ ፍሬ ውዳሴ ዐቢይ ዘርዐ ምሥጢር ሆኗል::

ይህንን ዐቢይ የእመቤታችን ውዳሴም ሚርስመን [Meerss-eman] የተባለው ምሁር "በጣም ጥንታዊና እጅግ ውብ ከሆኑትና በኦሬየንታል አብያተ ክርስቲያናት ሥርዓተ አምልኮ ዘወትር ከሚዘመሩት የድንግል ማርያም ምስጋናዎች ሁሉ የላቀና የታወቀ ውዳሴ ነው" ሲል ገልጾታል:: በመሆኑም "አካሲስቶስ" የሚለው ቃል የት መጣው የዕርዕ/የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጓሜ ምሥጢሩም አማንያን በምስጋናው ውስጥ ጎልቶ የሚታየውንና እንደ ዕንቁ ፈርጥ የሚያበራውን አምላካዊ የድኅነት ምሥጢር እያዩ፣ የወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በድኅነተ ዓለም ውስጥ ያላትን ልዩ ሱታፌ የሚያስተውሉበት ድንቅ ዝማሬ በመሆኑ ይህ መዝሙረ ድንግል ምእመናኑን በምስጋና ጊዜ እንዳይቀመጡ ይከለክላል::(403)

## 5.1.21 ወላዲተ አምላክ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው የመጀመሪያውን አምላካዊ ድንቅ ተአምር በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት እንዳደረገ በቅዱስ ወንጌል ተጽፎ እናገኛለን:: (ዮሐ. 2÷1-12) ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ለዚህ ልዩ አምላካዊ ተአምር ምክንያትና መሠረት የሆነው የቤዛዊተ ዓለም የድንግል ማርያም ምልጃ መሆኑንም አስረግጦ መስክሮ አል:: ይኸውም ርኅርኅተ ልቡና የሆነችው እመቤታችን በቃና ዘገሊላ

(402) Gambero, *Mary and the Fathers of the Church: The Blessed Virgin Mary in Patristic Thought,* 338-351. Palmer, *Mary in the Documents of the Church,* 54-56. Graef, *Mary: A History of Doctrine and Devotion,* 127-129. Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin,* 7. Graef, *The Devotion to our Lady,* 31-32.

(403) Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God,* 7-20.

ሠርግ የተዘጋጀው ወይን ባለቀ ጊዜ «ወይንኬ አልቦሙ፤ ወይን እኮ የላቸውም፣ የወይን ጠጅ አልቆባቸዋል» (ዮሐ. 2÷4) ስትል ለልጇ ለወዳጇ ለኢየሱስ ክርስቶስ ነገረችው:: ጌታችንም እናቱ ድንግል ማርያምን «ምንት ብየ ምስሌኪ ኦ ብእሲት ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜየ፤ አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ፣ ጊዜዬ ገና አልደረሰም» በማለት መለሰላት:: እመቤታችንም በሠርጉ በዓል ላይ ለነበሩት አገልጋዮች «ኵሉ ዘይቤለክሙ ግበሩ፤ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» ስትል በረከት የሚያገኙበትን ሥራ እንዲሠሩ አደረገቻቸው:: በዚሁ መሠረት እኒህ አገልጋዮች በሠርጉ ቤት የነበሩትን ስድስት ጋኖች ውኃ ሞሉአቸው:: ከዚህ በኋላ ገባሬ ተአ ምራት ወመንክራት የሆነው ጌታም ውኃውን ጣፋጭ ወደ ሆነ ወይን ለወጠው::

ከላይ በገለጥነው መሠረት በቃና ሠርግ ቤት የነበሩት ጋኖቹ ስድስት መሆናቸው አዳም በወደቀ ቢሉ በስድስት ሺህ ዘመን፣ ሠለስቱ ደቂቅ በባቢሎን እሳት ውስጥ በተጣሉ ቢሉ በስድስት መቶ ዓመት አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ ሰው ሆኖ አዳምን ከነልጆቹ ለማዳኑ ምሳሌ ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ የአምላክነት ሥራው ጌትነቱንና የባሕርይ ክብሩን በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት ገልጾአል:: ደቀ መዛሙርቱም ይህን አምላካዊ ድንቅ ተአምር አይተው እምነታቸውን ፍጹም በማጽናት ጌታን ተከትለዋል::

ይሁን እንጂ መምህረ ቅዱሳን የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ» (ማቴ. 22÷31) ብሎ እንዳስተማረው አንዳንድ የዋሃን ወገኖች መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያስረዳውን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን አማላጅነት ለራሳቸው ተጠራጥረው፣ ሌሎችንም ሲያጠራጥሩ ይስተዋላሉ:: ለዚህ የተሳሳተ አመለካከታቸው ደግሞ ከላይ የገለጥነውንና «አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም» (ዮሐ. 2÷4-5) የሚለውን ገጸ ንባብ



ይጠቅሳሉ:: ስለሆነም ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ «ንባብ ይቀትል ወትርጓሜ የሐዩ»፤ ገጸ ንባብ ይገድላል ማለትም ምሥጢሩ በቶሎ ስለማይረዳ ለግንዛቤ ያስቸግራል፣ ያዳግታል፤ በአንጻሩ ደግሞ ትርጓሜ ያድናል ማለትም የገጸ ንባቡን ምሥጢር አብራርቶና አፍታቶ ስለሚያስረዳ ከስሕተትና ከጥርጥር ያድናል ሲል እንዳስገነዘበው ከላይ የገለጥነውን የወንጌለ ዮሐንስ ገጸ ንባብ ምሥጢራዊ ትርጓሜ ቅዱሳት መጻሕፍትን አብነትና ማስረጃ በማድረግ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

### 5.1.21.1 «አንቺ ሴት» የሚለው ኃይለ ቃል ትርጓሜ

በመጽሐፍ ቅዱስ «ሴት» የሚለውን ቃል ትርጉም በኦሪት ዘፍጥረት 2÷21-23 ላይ እናገኛለን:: በዚህ ክፍለ ንባብ ሊቀ ነቢያት ሙሴ «እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም ጉን የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት:: አዳምም አለ፡- ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፤ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል::» ሲል ገልጾ አስረድቷል:: አባታችን አዳም ከሥጋው የተገኘችውን ሥጋ፣ ከአጥንቱ የተገኘችውን አካል ሔዋንን ሴት ብሎ መጥራቱ መገኛዋ እርሱ በመሆኑ ነው:: ስለዚህ ሴት ማለት ሥጋዋ ከሥጋዬ፣ ደሟ ከደሜ፣ አጥንቷም ከአጥንቴ ነው ማለት ነው::

በዚህ መሠረት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት (ዮሐ. 2÷4) እንዲሁም ራሱ በዕለተ ዓርብ የቀራንዮ ሙሽራ ሆኖ በታየባት በቀራንዮ መስቀል ላይ (ዮሐ. 19÷26) «አንቺ ሴት» ብሎ መጥራቱ በእርሷ በኩል የተፈጸመውን የተዋሕዶ ምሥጢር በግልጽ ያስረዳል:: ምክንያቱም መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ለድኅነተ ዓለም ሲል በተዋሕዶ የነሣው ሥጋና ነፍስ የእመቤታችን ነውና:: ስለዚህም ጌታችን እናቱ ድንግል ማርያም እሙ ለአምላክ፣ ወላዲተ አምላክ መሆኗን፤ እርሱም በተዋሕዶ ከእርሷ ባሕርይ

ፍጹም ሰው የሆነ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ሲያጠይቅ እናቱን "አንቺ ሴ ት" ብሏታል፡፡

ይህንን አስመልክቶ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ጣዕመ ፍቅሯና ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍ ሬም ሲመሰክር "... ከብካብ ንጹሕ ወመርዓ ቅዱስ፤ ድንግል ማርያም ሙሽራዋ ንጹሕ የሚሆን ንጹሕ የሠርግ ቤት ናት"(404) በማለት በምሥጢር አገናኝቶ ተናግሮላታል፡፡ ይህ የሊቁ ቃለ ውዳሴ የወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ሁለንተናዊ ክብርና ልዕልና ከመመስከሩም ሌላ እመቤታችን በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ልዩ ሱታፌና ከፍተኛ ሚና በግልጥ ያሳያል፣ ያረጋግጣልም፡፡

የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማን ይህን ቃለ ውዳሴ ከነገ ረ ድኅነት አስተምህሮ ጋር በማገናዘብ በምሥጢር አራቅቀው ተርጉ መውታል፡፡ ይኸውም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው የመጀመሪያውን ተአምር በሠርግ ቤት ማድረጉ በሥጋዌው አማካይነት የተፈጸሙትን አራት መሠረታዊ ምሥጢራትን ያስረዳናል፣ ያስገነዝበናል፡፡ እነዚህም:-

1ኛ) የመርዓዊ (የሙሽራ) እና የመርዓት (የሙሽሪት) መዋሐድ፣
2ኛ) አዝማደ መርዓዊ (የሙሽራ ወገኖች) እና አዝማደ መርዓት (የሙሽሪት ወገኖች) አንድነት፣
3ኛ) መብል መጠጥ፣
4ኛ) ጨዋታ፣ ተድላ ደስታ ናቸው፡፡

እንደሚታወቀው በሠርግ ቤት ከሚከናወኑት ከእነዚህ አራት መሠረታዊ ነገሮች የመጀመሪያውና ተቀዳሚው ቅድመ ጋብቻ (ከጋብቻ በፊት) ሁለት የነበሩት የመርዓዊና የመርዓት ተዋሕዶ (አንድነት) ነው፡፡ ጌታችን በወንጌለ መንግሥቱ "ወይከውኑ ክልኤሆሙ አሐደ ሥጋ፤ ናሁኬ

(404) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 84-85፡፡*



ኢኮኑ ፪ተ አላ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ፤ አንድ አካል ይሆናሉ፣ እነሆ ሁለት አይባሉም፤ አንድ አካል ናቸው እንጂ፡፡" (ማቴ. 19÷5-6) ብሎ እንዳስተ ማረ፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ረቂቅና ድንቅ በሆነው የሥጋዌ ምሥጢር ቅድመ ሥጋዌ ሁለት የነበሩት ትስብእትና መለኮት በተዋሕዶ አንድ መሆናቸውን በምሥጢር ያስተረጉማል፡፡

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ምሥጢራዊ ተዋሕዶ ሲያደንቅ "ዐቢይ ውእቱ ዝ ነገር፤ ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው"(405) ብሏል፡፡ (ኤፌ. 5÷32) በዚህ ሐዋርያዊ ትምህርቱም በመርዓዊና በመርዓት ተ ዋሕዶ አንጻር የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ የተፈጸመበትን አማናዊ የሥጋዌ ምሥጢር ገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም "እማን ዐቢይ እስመ ምክሩ ለዝንቱ ጽድቅ፡፡ ዝኬ ዘአስተርአየ በሥጋ ለብሰ፤ የዚህ የሥጋዌ ነገሩ እውነት እንደመሆኑ ደገኛና ታላቅ ምሥጢር ነው፡፡ ይኸውም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ የታየው መታየት ነው"(406) ሲል ድኅነተ ዓለም የተፈጸመበትን የተዋሕዶ ምሥጢር በአጽንኦት ተና ግሮአል፡፡ (1ኛ ጢሞ. 3÷16)

ሁለተኛው ደግሞ በሠርግ ቤት በሚፈጸመው የመርዓዊና መርዓት አንድነት ምክንያት አስቀድሞ ተራርቀው የነበሩ አዝማደ መርዓዊና አዝማደ መርዓት ይቀራረቡባታል፣ አንድ ይሆኑባታል፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ከወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን (ከሥጋዌ) አስቀድሞ ተለያይተውና ተራርቀው የነበሩት አዝማደ መለኮት (ቅዱሳን መላእክት) እንዲሁም አዝማደ ትስብእት (ደቂቀ አዳም) ግሩምና ድንቅ በሚያሰኘው የተዋሕዶ ምሥጢር አንድ ሆነዋል፡፡ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ "ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ ንጉሥ በቃለ አሚን፤ ምሥጢረ ተዋሕዶ በተገለጠባት በዚህች ንዕድና ክብርት ዕለት ሰማያውያን (ልዑላን) የሆኑ ሠራዊተ መላእክትና ምድራውያን (ትሑ ታን) የሆኑ ኖሎት (እረኞች) ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ

(405) *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው፣ ገጽ 290፡፡*
(406) *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው፣ ገጽ 362፡፡*

ፍጹም ሰው ሆኖ በኤፍራታ ቤተ ልሔም በእኛ ባሕርይ የተወለደውን እነሆ ንጉሥ ክርስቶስን በታመነ ቃል ያከብሩትና ያመሰግኑት ዘንድ እነሆ አንድ ማኅበር፣ አንድ መንጋ ሆኑ» ሲል የዘመረውም ይህንን አማናዊ ምሥጢር ለመግለጥና ለማስረዳት ነው።

ሦስተኛው ምሥጢራዊ ንጽጽር ደግሞ በሠርግ ቤት ሥጋዊ መብልና መጠጥ እንዲደረግ፤ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰው በሆነ ጊዜም «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖ ርም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ» (ማቴ. 4÷4)፤ «ለሚጠፋ መብል አትሥሩ» (ዮሐ. 6÷27) ብሎ ሕያውና ቅዱስ የሆነውን ቃሉን ምግበ ነፍስ አድርጐ ሰጥቶናል። ዳግመኛም «... የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም። ... ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። ... ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ።» (ዮሐ. 6÷35፣ 53-56)፤ «... መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሠርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች። ... እነሆ ድግሴን አዘጋጀሁ፣ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል÷ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሠርጉ ኑ...» (ማቴ. 22÷1-4፤ 26÷26-29)፤ «ወደ በጉ ሠርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው» (ራእ. 19÷9) ብሎ በተናገረው መሠረት ኅብስተ ሕይወት ቅዱስ ሥጋውንና ማየ ሕይወት ክቡር ደሙን ሰማያዊና ዘላለማዊ የሕይወት ማዕድ ይሆነን ዘንድ ምግበ ነፍስ አድርጐ በጸጋ ሰጥቶናል።

አራተኛውና የመጨረሻው አንጻራዊ ትርጓሜ ደግሞ በሠርግ ቤት የእድምተኞችን ልብ የሚመስጥና ደስ የሚያሰኝ ጨዋታና እልልታ ይደረጋል። እንዲሁም በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን በሰማይና በምድር ያሉ ፍጥረታት ሁሉ ፈጽመው በመደሰታቸው «ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም፣ ዮም ተወልደ ክሣቴ ብርሃን፣ ዮም ተወልደ መድኃኔዓለም» እያሉ



በአንድነት የሚዘምሩና የሚያመሰግኑ ሆነዋል። ዳግመኛም ሰማያውያን መላእክ ትና ምድራውያን ኖሎት የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ አማናዊ ሆኖ በተገለጠባት ክብርት ዕለት «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ፤ ክብር ለእግዚአብሔር በሰማይ ይሁን፤ ሰላምም በምድር ለሰው ልጆችም በጎ ፈቃድ ይሁን» (ሉቃ. 2÷14) በማለት ልዩ የሆነ አዲስ ምስጋና አቅርበዋል።

ከዚህም ጋር ታላቁ የጌታ መልአክ በዕለተ ልደት መንጋቸውን በሌሊት ነቅተውና ተግተው ሲጠብቁ ላደሩ እረኞች «እነሆ÷ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና» (ሉቃ. 2÷10-11) ሲል የሰበከው ቃለ ብሥራትና ቃለ ፍሥሐ መርዓዊ (ሙሽራው) ክርስቶስ ከመርዓት (ሙሽራይቱ) እስራኤል ዘነፍስ ጋር በተዋሕዶ አንድ የሆነበትን ታላቅና ድንቅ የሥጋዌ ምሥጢር ያስረዳል፣ ያስገነዝባል። ቃለ ዓዋዲ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ «ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው» (ዮሐ. 3÷29) ብሎ እንደመሰከረ።

መድኅነ ዓለም ክርስቶስ የመጀመሪያውን ተአምር በእናቱ በድንግል ማርያም አማላጅነት በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት የማድረጉ ምሥጢር ከነገረ ድኅነት ጋር ያለው ሌላው ግንኙነት ደግሞ ኃጢአትና በደል፣ ሞትና መርገም ወደ ዓለም የገባበትን የስሕተትና የድቀት በር ለመዝጋት ነው። ይኸውም የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን ሠናዬ ሕግ የሆነው አምላክ ባርኮና ቀድሶ አክብሮ የሰጣቸውን የጋብቻ ጽምረት (ኅብረትና አንድነት) አጽንተው ባለመጠበቃቸው ምክንያት በምክረ ከይሲ ተታልለው ወድቀዋል። በሌላ አገላለጽ እናታችን ሔዋን ፈጣሪዋ እግዚአብሔር ወዶና ፈቅዶ፣ ባርኮና ቀድሶ ከሰጣት አካል (ከአዳም) ጋር የነበራትን የትዳር ጓደኝነት (አንድነት) ትታና ረስታ እግዚአብሔር ካልፈቀደላትና ካልሰጣት ሌላ ባዕድ አካል (እባብ) ጋር

በመወዳጀቷ ኃጢአትንና ሞትን አምጥታለች:: (ዘፍ. 3÷1-5) በአንጻሩ ደግሞ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመለኮትና ለትስብእት አንድነትና ተዋሕዶ ምሳሌ የሆነው የመርዓዊና የመርዓት ተዋሕዶ በተደረገበት በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ተገኝቶ የጌትነቱን ሥራ መሥራቱና የአምላክነቱን ምሥጢር መግለጡ ለቀደመው የአዳምና የሔዋን ስሕተትና በደል ካሣ መሆኑን ልብ ይሏል::[407]

ከላይ የገለጥነው ምሥጢራዊ ትርጓሜ በቀዳሚት ሔዋን ምክንያት በሰው ዘር ላይ የተላለፈው መርገምና የሞት ፍርድ በዳግሚት (አዲሲቷ) ሔዋን በድንግል ማርያም አማካይነት እንደቀረና እንደተሻረ በማረጋገጥ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሰፊ ድርሻና መሠረታዊ ሚና በግልጥ ያስረዳል፣ ያስገነዝባልም:: በመሆኑም አበው "ወድቀው ይነሢል በእጅ ዘግይተው ይከብሯል በልጅ" እንዲሉ በቀዳሚት ሔዋን ስሕተት ምክንያት በኃጢአት ወድቆ፣ ከፈጣሪው ርቆ፣ ከክብሩም ተዋርዶ የነበረው የሰው ሕይወት በኋለኛው ዘመን ወለተ ሔዋን በሆነችው በዳግሚት ሔዋን በቅድስት ድንግል ማርያም አማካይነት ከድቀተ ኃጢአቱ በመነሣቱና አጥቶት የነበረውን ልጅነት፣ ጸጋና ክብር ዳግመኛ በማግኘቱ እመቤታችን ጠሠራቲ ሕይወት፣ ምክንያተ ድኅነት ሆነች::

በዚህም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር "በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ:: እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ" (ዘፍ. 3÷15) ሲል አስቀድሞ የሰጠው ተስፋ ድኅነት በድንግል ማርያም በመፈጸሙ ቅዱሳት መጻሕፍት በመተባበር እመቤታችንን "ሴት" እያሉ

(407) ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ፣ [Emperor Zara Yacob]፣ *መጽሐፈ ብርሃን፣ ["The Book of Light"] CSCO,* 84-87. Galot, *Mary in the Gospel,* 104-111, 274-276. Sheen, *The World's First Love,* 117-120. Bauer. *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers,* 53-54. Russell, "The Blessed Virgin Mary in the Bible: The Scriptural Basis of Ecumenical Dialogue", 48-49. *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 460-461::



የሚጠሩበትን ዐቢይ የድኅነተ ዓለም ምሥጢር በግልጽ መረዳትና መገንዘብ ይቻላል::

ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም የዚህን ተስፋ ድኅነት ፍጻሜ አስመልክቶ ሲናገር "ወአመ በጽሐ ዕድሜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት፤ ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፤ ከሴትም ተወለደ" (ገላ. 4÷4) በማለት መስክሮአል:: ዳግመኛም ከዚህ ሁሉ ሐተታና ትርጓሜ ለመዳን እመቤታችን ድንግል ማርያም ሴት ስትሆን ልማደ አንስት አልደረሰባትምና አዋልደ ኢየሩሳሌም 'ኃይል አርያማዊት' ይሏት ነበር:: ስለዚህም እመቤታችን በአማን ወለተ አዳም ወሔዋን የሆነች ሴት እንደሆነች ለማስረዳት "አንቺ ሴት" አለ::

ከዚህም ጋር በቀዳሚት ሴት በሔዋን ምክንያት የመጣው ስሕተትና መርገም አማናዊት እመ ሕያዋን በመሆንችው በዳግሚት ሔዋን በእመቤታችን እንደተደመሰሰ ለማጠየቅ "አንቺ ሴት" ሲል ገልጿታል:: ስለሆነም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት (ዮሐ. 2÷4)፤ እንዲሁም በቀራንዮ መስቀል ላይ ሳለ (ዮሐ. 19÷26) "አንቺ ሴት" ብሎ መጥራቱ ከላይ ከጠቀስነውና በቅድስት ኦሪት ከተነገረው አምላካዊ ተስፋ ድኅነት ጋር በምሥጢር የተገናዘበና የተሰናሰለም መሆኑን ይመሰከቷል::

በመጨረሻም "አንቺ ሴት" የሚለው አነጋገር የዕብራውያን የአነጋገር ዘይቤ በመሆኑ የአገሩን ባሕልና የሕዝቡን ልማድ የሚያመለክት እንጂ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ከዚህ የወጣ የንቀት ወይም ያጥላቻ አልያም ደግሞ የማቃለል አነጋገር አይደለም:: ለዚህም "አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው እንደወደድሽ ይሁንልሽ" (ማቴ. 15÷28) ሲል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም እምነትና ትሕትና ወደ እርሱ ዘንድ ለመጣችው ለከነናዊቷ ሴት የተናገረው ቃለ አክብሮ፤ ዳግመኛም "አንቺ ሴት እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ?" (ዮሐ. 8÷10) ሲል በይቅር

ታውና በምሕረቱ የተቀበላትን ኃጢአተኛ ሴት መጠየቁ፤ እንዲሁም በዕለተ ትንሣኤው "አንቺ ሴት ስለምን ታለቅሻለሽ?" (ዮሐ. 20÷13)፤ በማለት ቅዱሳን መላእክትና ራሱ የትንሣኤው ባለቤት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ መግደላዊት ማርያምን ማነጋገራቸው በቂ ማስረጃና ምስክር ነው::[408]

ስለሆነም በእነዚህ ቃላተ መጻሕፍት ማስረጃነት "አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ?"፣ "አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ" የሚለው አባባል በእስራኤላውያን ዘንድ በስፋት የታወቀና የሚሠራበት አክብሮታዊ የአነጋገር ዘይቤ መሆኑን መረዳትና መገንዘብ ያስፈልጋል::

### 5.1.21.2 "ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?" የሚለው ገጸ ንባብ ትርጓሜ

በመጽሐፍ ቅዱስ በስፋት እንደተገለጸው "ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ከአንተ ጋር ምን አለኝ?" የሚለው አነጋገር በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ፍጹም አክብሮትንና ትሕትናን የሚገልጽ እንጂ ከዚህ የወጣ ሌላ ትርጉም ፈጽሞ የለውም:: ለምሳሌ ያህል ብንመለከት በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17÷18 ላይ የሰራፕታዋ መበለት (የነቢዩ ዮናስ እናት) ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስን "የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ኃጢአቴንስ ታሳስብ ዘንድ ልጄንስ ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃልን? አለችው" ተብሎ ተጽፏል:: ታዲያ በዚህ ገጸ ንባብ መሠረት የሰራፕታዋ ሴት የእግዚአብሔር ሰው ኤልያስን የተናገረችው በፍጹም አክብሮትና ትሕትና ነው? ወይስ በንቀትና በጥላቻ? ስለዚህም ይህ ዘይቤያዊ አገላለጽ ፍጹም ትሕትናንና አክብሮትን የተመላ አነጋገር እንጂ ሌላ አለመሆኑን ማስተዋል ይገባል::

ዳግመኛም በማቴዎስ 8÷29 ላይ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ጌርጌሴኖን አገር በመጣ ጊዜ

[408] አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ ክብረ ድንግል፣ ገጽ 6::



አጋንንት "ኢየሱስ ሆይ የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታጠፋን /ልታሰቃየን/ ወደዚህ መጣህን? እያሉ ጮኹ" በማለት ገልጾአል:: ታዲያ እንደ አንዳንዶች አባባል "አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ?" የሚለው ገጸ ንባብ የጥላቻና የንቀት አነጋገር ነው ከተባለ በዚህ ዓውደ ንባብ መሠረት አጋንንት የባሕርይ አምላክ ወልደ እግዚአብሔርን ናቁት፣ ሰደቡት፣ አቃለሉት፣ ዘበቱበት ሊባል ነውን? በፍጹም! ይህማ እንዳይባል አጋንንት እንኳን በኃያሉ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ሊሳደቡ ይቅርና እርሱን አምነው፣ በፈቃዱ ጸንተው በሚኖሩ ምእመናን ፊት እንኳን መቆም አይቻላቸውም:: (መዝ. 90÷1-7፤ ማቴ. 10÷1፤ ሉቃ. 9÷1-2፤ 10÷47፤ 1ኛ ጴጥ. 5÷8-9፤ ያዕ. 4÷7-8) ስለዚህም ከዚህ ገጸ ንባብ አጋንንት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በታላቅ ፍርሃትና በፍጹም አክብሮት ፈርተውና ተንቀጥቅጠው "ጌታ ሆይ ካንተ ጋር ምን አለን?" ብለው እንደለመኑት ልብ ይሏል::

እንግዲህ በአጭሩ ከላይ በገለጥናቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት "አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?" (ዮሐ. 2÷4) የሚለው ገጸ ንባብ እናቴ ሆይ የምትጠይቂኝን ላላደርግልሽ፣ የምትለምኚኝን ነገር ሁሉ ላላፈጽምልሽ ከአንቺ ጋር ምን ጠብ፣ ምንስ ክርክር አለኝ? አንድም በእኔና በአንቺ መካከል ምን ችግር አለ? ማለት መሆኑን ማስተዋል ይገባል::[409] ዳግመኛም ይህ ገጸ ንባብ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን በፍጹም ትሕትና እንዳነጋገራትና ፍጹም በሆነ አክብሮታዊ ቃል እንደመለሰላት ያስረዳል እንጂ ከዚህ የወጣ ሌላ ፍቺና ትርጉም የለውም:: ይህም ይታወቅ ዘንድ ሠዝገበ በረከት የሆነችው እመቤታችን "ወይን እኮ የላቸውም" ስትል ለልጇ ለወዳጇ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያቀረበችው ጥያቄ ተፈጽሞላታል::

[409] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 459-461:: አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ ክብረ ድንግል፣ ገጽ 6::



**ሥዕል 14፡- ወላዲተ አምላክ በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት**

"ኦ ድንግል አዘከሪ ኀበ መዘከር ዘኢይረስዕ ኵሉ፤ ድንግል ሆይ ከሚያስብ ሁሉን ከማይዘነጋ ከልጅሽ ዘንድ አሳስቢ"

(መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 190)

ማርያም ድንግል ለነዳይ ንዋዮ ወርቁ፣
እመ ነገደ ርኁቀ ወሖረ ሰፊቁ፤
ኢይኅዝኖ ሲሳይ እስመ አንቲ ስንቁ።

(መልክአ ማርያም፣ ገጽ 525)



## 5.1.21.3 "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" የሚለው ኃይለ ቃል ትርጓሜ

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት የወይን ጠጅ እንዲሰጥ እናቱ ድንግል ማርያም በጠየቀችው ጊዜ "ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜየ፤ ጊዜዬ ገና አልደረሰም" (ዮሐ. 2፥4) ሲል መልሶላታል። የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ መምህራን ጌታችን ይህን ኃይለ ቃል ስለ አራት ነገሮች እንደተናገረ አስረድተዋል።(410) ይኸውም፡-

የመጀመሪያው ምክንያት የሥራ አምላክና የጊዜ ባለቤት የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራውን ሁሉ የሚሠራበትና ፈቃዱንም የሚፈጽምበት የራሱ ጊዜ እንዳለው ለማጠየቅ ነው። ይህንን አስመልክቶ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ሲናገር "ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር፤ ልዑል ባሕርይ እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ አለው" (መዝ. 118፥126) በማለት መስክሮአል። ከዚህም ጋር ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፤ ከሴትም ተወለደ" (ገላ. 4፥4) በማለት በአጽንኦት አረጋግጧል።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እመቤታችን "የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም" የሚለውን ጥያቄ ባቀረበችበት ጊዜ በጋኖቹ ውስጥ የነበረው ወይን ገና ፈጽሞ አላለቀም ነበርና ጌታችን "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" አላት። ይኸውም ምሥጢሩ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስን የሚያድለው ጌታ በጋኖቹ ውስጥ የነበረውን ተረፈ ወይን ብቻ አበርክቶ ሰጥቶ ቢሆን ኖሮ ተአምራቱ ፈጽሞ ባልተደነቀም ነበር። በአንጻሩ ግን ጋኖቹ ፈጽሞ ባዶ ከሆኑ በኋላ እምኀበ አልቦ

(410) ቅዱስ ወንጌል ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 459።

(ከምንም) አምጥቶ ማስገኘትና መስጠት የአምላክነት ግብር ብቻ በመሆኑ አምላክነቱ፣ ጌትነቱ፤ የባሕርይ ክብሩ ይገለጥ ዘንድ ይህን አለ።

ሦስተኛው ምክንያት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም "ወይን እኮ የላቸውም" የሚለውን ልመና ለልጇ ባቀረበችበት ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የሚሆን የአስቆሮታዊው ይሁዳ ከሠርጉ ቤት ወጣ ብሎ ነበርና እስኪመለስ ድረስ ጌታችን "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" አለ። ምክንያቱም ይህ ይሁዳ ኋላ በጸሎተ ሐሙስ ምሽት በትእምርተ ስዒም (በመሳም ምልክት) ጌታውን አሳልፎ ለመከራና ለሞት የሚሰጠው ነውና ከተአምራቱ ቢለየኝ ከሞቱ ገባሁበት እንዳይል ምክንያት ለማሳጣት ነው። ይህንን ራሱ ባለቤቱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር "አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም" (ዮሐ. 15÷22) ሲል አስገንዝቦአል።

አራተኛውና የመጨረሻው ምክንያት ደግሞ ቀደም ብለን እንደገለጥነው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀ መሪያውን ተአምር በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት ያደረገው በሥጋዌው ምሥጢር የሚፈጽመውን የቤዛነት ሥራና በዚህም ለሰው ልጆች የሚሰጠውን የድኅነት ጸጋ ለመግ ለጥ መሆኑን ተመልክተናል። ስለሆነም የቀራንዮ ሙሽራ ኢየሱስ ክርስቶስ "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" ማለቱ ሕማናዊውን ወይን ማለትም ማየ ሕይወት ደሙን በመስቀል ላይ ለዓለም ሁሉ የሚሰጥበት (የሚያፈስበት) ጊዜ ገና መሆኑን ሲያጠ ይቅ ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ ጌታችን የቤዛነቱን ሥራ የሚፈጽምበት ጊዜ ሲደርስ ለደቀ መዛሙርቱ "የሰው ልጅ



ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሶአል። እውነት እውነት እላችኋ ለሁ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች" (ዮሐ. 12÷ 23-24) ሲል በምሥጢር ገልጾ ነግሯቸዋል።

ከዚህም ጋር የድኅነተ ዓለም ተስፋ የሚፈጸምበት ሰዓት ሲደርስ "በመሸም ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር በማዕድ ተ ቀመጠ። ... ጽዋውን አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፦ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው። ነገር ግን እላችኋለሁ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሮ አልጠጣውም" (ማቴ. 26÷20፣ 27-29) ብሎ በተናገ ረው አምላካዊ ቃለ በረከት አማካይነት መሥዋዕተ ወንጌል (ምሥጢ ረ ቁርባን) ተመሥርቷል።

እመቤታችን ድንግል ማርያም ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ "ወእሙሰ ተዓቅብ ዘንተ ኵሎ ነገረ። ወትወድዮ ውስተ ልባ፤ እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር" (ሉቃ. 2÷51) ብሎ እንደተናገረው የልጇ የወዳጇ የኢየሱስ ክርስቶስ ቋንቋ በቶሎ የሚገባት የበረከት እናት፣ የምሥጢር መዝገብ በመሆኗ በሠርጉ ቤት የነበሩትን አገልጋዮች "ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ፤ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" (ዮሐ. 2÷5) ብላ አሳሰበቻቸው። በዚህም መርሐ ቃል መሠረት መዝገበ በ ረከት፣ መራሒተ ፍኖት የሆነችው እመቤታችን ወደ ልጇ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ ጸጋና በረከት መርታ አደረሰቻቸው (ሥዕል 11 ይመልከቱ)። ሌላው ምሥጢር ደግሞ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድን ድኅረ ዓለም ያለ አባት በሥጋ የወለደችው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በገሊላ ቃና "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" ማለቷ በፈለገ ዮርዳኖስና በደብረ ታቦር "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" (ማቴ. 3÷17፤ 19÷5) ሲል የተናገረውና ቅድመ

ዓለም ያለ እናት ከባሕርዩ የወለደው የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ እንደሆነችም ያጠይቃል::(411)

ርኅርኅተ ኅሊና የሆነችው ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በዚህ ምልጃዋና ርኅራኄዋ ልቡናችንን ዘወትር በጎ ወደሆነው ወደ ልጇ ፈቃድ የምትመራን የማትሰበርና የማታዘነብል አማናዊት በትረ ሃይማኖታችን ናት:: ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴው «በትረ ሃይማኖት ዘኢትጸንን ምስማኮሙ ለቅዱሳን፤ የማትለወጥ የቅዱሳን ሃይማኖታቸው አንቺ ነሽ»(412) ሲል እንዳመሰገናት:: ስለሆነም ወላዲተ አምላክ በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት ያደረገችው ምልጃ ባዶ የነበሩት ጋኖች ጥዑም በሆነ ወይን እንዲመሉ ከማድረጉም በላይ ደቀ መዛሙርቱም እምነታቸውን እንዲያጸኑ አስችሏቸዋል::

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ይህንን አስመልክቶ ሲናገር «ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፣ ደቀ መዛመርቱም በእርሱ አመኑ» (ዮሐ. 2÷11) ብሏል:: ይህም ማለት መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በእመቤታችን በድንግል ማርያም ልመናና አማላጅነት የጌትነቱን ሥራ ሠርቶ የአምላክነቱን ምሥጢር በገለጠ ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ንቁ÷ በሃይማኖት ቁሙ÷ ጎልምሱ ጠንክሩ» (1ኛ ቆሮ. 16÷13) ሲል እንዳስገነዘበው ደቀ መዛሙርቱ እምነታቸውን የበለጠ ማጽናታቸውንና ማጠንከራቸውን መናገር ነው::

ይህንን ታላቅ ምሥጢር አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋና «ሰአሊ ለነ ኀበ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ:: ያጽንዓነ በርትዕት ሃይማኖት ውስተ አሚነ ዚአሁ፤ የባሕርያችን መመኪያ፣ አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ

(411) Laurentin, *Hail Mary: Its Meaning and Its Origin*, 57-58. Galot, *Mary in the Gospel*, 153-154. Nouwen, *Behold the Beauty of the Lord: Praying with Icons*, 32, 40. መዝሙረ ድንግል፣ ገጽ 6፣ 59::

(412) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 180::



አንድነቱን ሦስትነቱን፤ አንድም ሥጋዌውን በማመን በቀናች ሃይማኖት ያጸናን ዘንድ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ለምኝልን፣ አማልጅን»(413) በማለት ሰዓሊተ ምሕረት፣ ምዕራገ ጸሎት የሆነችው ድንግልን በታመነው ልመናዋና አማላጅነቷ ይማጸናታል::

በመሆኑም ኦርቶዶክሳውያን ሠዓልያን [Orthodox Iconographers] ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በቃል ኪዳኗ ለሚማፀኑና በአማላጅነቷም ለሚታመኑ ሁሉ መራሒተ ልቡና መሆኗን የቅዱሳት ሥዕላት ሊቃውንት «መራሒተ ፍኖት» ወይም *Hodegetria* - "She Who Shows the Way" ወይም በግሪኩ [Όδηγε] በተሰኘው ኦርቶዶክሳዊ የእመቤታችን ሥዕል (ምስለ ፍቁር ወልዳ) አማካይነት በስፋት ይገልጻሉ:: በዚህ ሥዕል ላይ እንደምንመለከተው ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ቀኝ እጇን ወደ ተወዳጁ ልጇ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደዘረጋች ያሳያል:: ትርጓሜ ምሥጢሩም መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት የተባለች እመቤታችን ወደ ልጇ፣ ወደ ወዳጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወትር የምትመራን የበረከት እናት መሆኗን ይገልጻል::

ከዚህም ጋር የእመቤታችን ሁለንተናዊ ሕይወት ከክርስቶስ የማዳን ሥራ ጋር በእጅጉ የተዋሐደ መሆኑን በመግለጥ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ዐቢይ ድርሻና ጉልህ አስተዋጽኦም አስረግጠ ይመሰክራል::(414) በመጨረሻም እመቤታችን ድንግል ማርያም በገሊላ ቃና ሠርግ ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መጠራቷ (ዮሐ. 2÷1-2) በምስጋናችን፣ በመዝሙራችንና በቅዳሴያችን ሁሉ የእርሷ ሕይወት ከልጇ የማዳን ሥራ ጋር በእጅጉ የተዋሐደና ፈጽሞ የማይለይ መሆኑን በምሥጢር ያስተረጉማል::

(413) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 205-206:: Daniel, *Blessed Virgin Mariam*, 137. ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 460-461::

(414) Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality*, 117. Hainsworth, "The Ever-Virginity of the Mother of God," 16. Mascall, "The Mother of God," 173, 180-181, 191. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 47, 51, 55. Galot, *Mary in the Gospel*, 157-158.